# <u>መንፈሳዊ ፍሬን ማፍራት</u>

## <u>መግቢያ</u>

- ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ባስገዛን ወይም በሰጠን መጠን የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን መታየት ይጀምራል (ገላ 5፣22-23)
- የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን ውስጥ ተገለጠ ማለት ክርስቶስን የሚመስል ባህሪ ለሁሉ እያሳየን እንመላለሳለን ማለት ነው

## <u>መንፈሳዊ ፍሬን ለማፍራት የሚቻለው እንዴት ነው?</u>

- እግ/ር የፈጠራቸው ተክል በሙሉ እንደ ዝርያቸው ዐይነት ፍሬን እንደሚሰጡ ሁሉ ክርስቲያንም ደግሞ መንፈሳዊ ፍሬን <u>በመንፈስ ቅዱስ</u> አማካኝነት ያፈራል
- አማኝ ከክርስቶስ ጋር ያለውን እውነተኛ ግንኙነት የሚታወቀው በሚያፈራው የመንፈስ ወይም የስጋ ፍሬ አይነት ነው (ማቴ 7፣15-23)
- ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ቅዱስ ባህሪውን መግለጡ በሰው ድካም የሚገኝ አይደለም
- ክርስቲያናዊ ፍሬን ኮርጆ በትክክል እንደዚያ መሆን <u>ፈጽሞ</u> አይቻልም

## <u>ፍሬ ለማፍራት አስፈላጊ ሁኔታዎች</u>

### 1. በክርስቶስ ውስጥ መኖር

- " በእኔ ኑሩ " (ዮሐ15፣4) ይህ ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነትና ስፍራ ያመለክታል (2ቆሮ 5፣17)
- ቅርንጫፍ ከወይኑ ግንድ ጋር እንደሚያያዝ ሁሉ አማኝም እንዲሁ በክርስቶስ ጋር መጣበቅና መያያዝ አለበት (ዮሐ15፣4)
- የበዛና የሻለ ፍሬ የሚገኘው ቅርንጫፉ ከወይኑ ግንድ አስፈላጊ ንጥረ ነገሮች ሲመጡለት ብቻ ነው። አማኝም እንዲሁ ሊያፈራ የሚችለው በክርስቶስ ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው

### 2. ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲኖር

- " እኔም በእናንተ " (ዮሐ15፣4) ክርስቶስ በእኛ ሲኖር ብቻ ነው ፍሬያማ ወይም ክርስቶስን የሚመስል ባህሪ ማሳየት የምንችለው
- ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲኖር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የእርሱን ማንነት በፍሬያችን እናንጸባርቃለን <u>ምሳሌ</u> - ሐዋ/ ጳውሎስ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት በክርስትና ኑሮውና አገልግሎቱ ያንጸባርቅ ነበር (1ኛ ቆሮ 11፣1)

## <u>ፍሬያማ ለማድረግ የሚረዱ ነገሮች</u>

- አማኝ ፍሬያማ እንዲሆን፣ ኢየሱስ በእርሱና በአማኝ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት ለመግለጽ ስለ ወይኑና ቅርንጫፎቹ ምሳሌ ተጠቀመ (ማቴ15፣1-17)
- በወይኑ ግንድ ላይ በጣም አስፈላጊው ነገር <u>ወይኑ የሚያፈራው ፍሬ ነው</u>
- ገበሬው (አብ) የተዋጣለት ፍሬ ለማግኘት ሲል የሚከተሉት ስራዎችን በወይኑ ላይ ያከናውናል

### 1. ፍሬ የማያፈራውን ቅርንጫፍ ማስወገድ (ዮሐ15፣2)

- ቅርንጫፍ በግንዱ ላይ የመኖሩ ትርጉም ፍሬ ማፍራቱ ላይ ነው ለለዚያ ገበሬው(አብ) ያስወግደዋል። <u>ምሳሌ</u>- የእስራኤላዊያን ታሪክ - (ኢሳ 5፣1-7)
- እንዲሁ ደግሞ በክርስቶስ ሆኖ ፍሬ አለማፍራት የሚያስጠይቅ ሕይወት ነው። <u>ለምሳሌ</u> - የእስራኤላዊያን ታሪክ (ኢሳ 5፣1-7)

2. **ከወይኑ ግንድ ጋር ያልተጣበቁ ቅርንጫፎችን ሰብስቦ በእሳት ማቃጠል (ዮሐ15፥4)**
   - ከወይኑ ግንድ ጋር ያልሆኑ ቅርንጫፎች ሁሉ ወደፊት ፍሬ ማፍራት ስለማይችሉ ይቃጠላሉ
   - ክርስትና ራስን ለክርስቶስ መስጠትና ከእርሱም ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ማድረግ ነው። <u>ለምሳሌ</u> - ቅርንጫፍ በግንዱ ላይ ሳለ ሲሰበር መልኩን በተለያየ ሁኔታ ከቀያየረ ቦኃላ ይሞታል። ስለዚህ እርሱን ማስወገድና ማቃጠል ያስፈልጋል

3. **ፍሬ የሚያፈራውን ቅርንጫፍ ደግሞ መግረዝ (ዮሐ15፥2)**
   - ቅርንጫፎችን መግረዝ አስፈላጊነቱ ለምንድን ነው? <u>የበዛና የተሻለ</u> ፍሬ እንዲገኝ ነው። እንዲሁ ደግሞ በእ/ር የሚደረግ ግርዘት <u>እርሱን የመምሰል ሕይወትን</u>፣ <u>ቅድስናን</u> ፣ ወዘተ ያጎናጽፈናል
   - ከግንዱ የሚተላለፉውን ሕይወት ሰጪ ንጥረ ነገሮች ወደ ፍሬ እንጂ ጥቅም ወደሌለው ነገር እንዲለወጥ ገበሬው (አብ) አይፈቅድም
   - አማኝ ዳግም ከተወለደ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በእግ/ር ቃል አማካኝነት ክርስቶስን የማይመስሉ አመለካከቶችንና ባህሪያቶችን ከውስጣችን የማጥራት ስራ ይሰራል
   - በእድገት ሂደት ውሰጥ መንፈሳዊ ግርዘት <u>የክርስትያንን ባህሪ</u> ያጎለብታል

## <u>መንፈሳዊ ፍሬ የማፍራት ዐላማ</u>

1. **የክርስቶስን ሕይወት ለመግለጥ ነው**
   - ማንኛውም ፍሬ ያለበት ተክል የሕይወት መገለጫ እንዳለው ሁሉ እንዲሁ ደግሞ የክርስቶስ አካል የሆነ ብልት የእርሱን ባህሪ በሙላት መግለጥ መቻል አለበት
   - አማኝ ዋነኛ ተግባሩ ክርስቲያን መሆን ብቻ ሳይሆን <u>ሌሎች</u> ክርስቶስን ማየት እንዲችሉም ጭምር ነው

2. **የደቀመዝሙርነት ማስረጃ ነው**
   - የክርስቶስ ደቀመዛሙርት የሚታወቁት በሚያፈሩት <u>ብዙ ፍሬና ዓይነት</u> ነው (ዮሐ15፥8)
   - በሚገባ የተማረ ማንኛውም ደቀመዝሙር ልክ እንደ መምህሩ እንደሚሆን ጌታ ተናግሯዋል (ሉቃ 6፥40)
   - ጌታን ከመቀበል ባሻገር አማኞች በፍሬያቸው ከክርስቶስ ወገን መሆናቸውን ሊያስመሰክሩ ይገባል

3. **እ/ርን ለማክበር ነው**
   - መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት የተትረፈረፈ ሕይወት ውጤት ነው
   - ሰዎች ይህንን ውጤት በመመልከት እ/ርን ያከብራሉ (ዮሐ15፥8, ማቴ 5፥16)

4. **ለሌሎች በረከት ለመሆን ነው**
   - በመጀመሪያ ደረጃ በሕይወታችን ለተገለጠው የክርስቶስ ባህሪ ተጠቃሚ ለሆኑት ሁሉ በረከት እንሆናለን
   - ከዚያም አልፎ ሕይወታችንን ለሚያዩት ሁሉ በረከት መሆን እንችላለን

## <u>አማኞች መንፈሳዊ ፍሬን እንዲያፈሩ የሚያበቁ ነገሮች</u>

- ፍሬ የሚያፈሩ ተክሎች ሁሉ ብዙ ፍሬ ሊያፈሩ የሚችሉት ትክክለኛ እንክብካቤ የተደረገላቸው እንደሆነ ነው
- ይህ መርህ እንዲሁ ደግሞ መንፈሳዊ ፍሬን ለማፍራት የሚሰራ እውነት ነው
- በመጀመሪያ አበባ ከዚያም የፍሬ ምልክቶች እስኪታዩ ድረስ እንክብካቤና አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ይገባል

## አማኝ በመንፈስ ቅዱስ በመታገዝ በሚከተለው ሁኔታ ፍሬ ማፍራትና ራሱን ማሳደግ ይችላል

1. ከእ/ር ጋር የምናደርገውን ኅብረት በመጨመር
    - ሕይወታችን የሚለወጠውና ፍሬ ወደ ማፍራት የሚያድገው የማያቋርጥ ኅብረትና ግንኙነት ከእ/ር ጋር በማድረግ ነው
    - ይህንን ኅብረት በአምልኮ፣በጸሎት፣በእ/ር ቃል በመታገዝ ልናሳድገው እንችላለን
    - ከእርሱ ጋር በሚኖረን ጤናማ ግንኙነት የተነሳ ሕይወታችን ፍሬያማ ይሆናል (ዮሐ15፣7; 9-10)

2. ከሌሎች አማኞች ጋር የሚኖረንን ኅብረትና አንድነት በማሳደግ
    - ተመሳሳይ ተክሎች በአንድ እርሻ ቦታ ላይ እንደሚሆኑ ሁሉ <u>በክርስቲያናዊ ኅብረት መያያዝ</u> ከፍተኛ የሕይወት እድገትን ያመጣል (ሐዋ 2፣46)

3. እ/ር በሰጠን ልዩ ልዩ ጸጋ እርስ በርሳችን መገልገል ስንችል
    - ከእ/ር የተቀበልነውን መልካም ነገር ሁሉ በሚያስፈልገው ቦታ ስንተገብረው ብዙ ወደምናፈራበት ሁኔታ እንመጣለን (1ቆሮ 3፣6)

4. በንቃት ስንኖርና ክፉን ለመከላከል ስንበቃ
    - ምንጊዜም አትክልትን የሚጎዱ አደጋዎች እንዳሉ ሁሉ የአማኝንም ሕይወት ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ልናውቃቸውና ልንከላከላቸው ይገባል
    - መጥፎ ልማዶች፣የተሳሳቱ አመለካከቶችና ቁርኝቶች፣አፍራሽ እሳቤዎችና የተሳሳቱ ፍላጎቶች ሁሉ መንፈሳዊ እድገትን የሚጎዱ መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል